Y.CEOPO Postfach 102409, 60024 Frankfurt – Germany, e-Mail CEOPO@T...online.de TEL./FAX: +49-69 37108840

# ከአንጃዎች ትርምስና ከክፍተቱ ስበብ ባሻገር

ከሁለት ወራት ጀምሮ ባንድ በኩል በህወሃት ውስጥ የተከሰተው ያንጃዎች ግጭትና በሌላ በኩል የሃገራችን ወጣቶች ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸውን ለማስከበርና ሌሎችም ህዝባዊ ጥያቄዎችን በማንሳት በአገራችን በአራቱም ማእዘናት ተጋግዘው መነሳታቸው ሃገራችንን አዲስ የትግል ምእራፍ ውስጥ አስገብትዋታል፣፣ የነአቶ መለስ ዜናዊ አንጃ ከህወሃት ክፍፍል ውጥረት ሳይወጣ የዚህን ጸረ ህዝብ የከፋፍለህ ግዛ ሴራ አክሽፈው የኢትዮጵያ ወጣቶች ከመቀሌ እስከ አርባ ምንጭ፣ ከጅማ እስከ አዋሳ የአዲስ አበባ ዩኒበርሲቲ ተማሪዎች የዴሞክራሲ ትግል ደግፈው በመንቀሳቀሳቸው እንደአበደች ውሻ ዙሪያውን የመናከስ ፖሊሲ በመምረጡ በከተማይቱ ልዩ ኮማንዶ በማሰማራት በሃገራችን ወጣቶች ላይ ይህ ነው የማይባል ወንጀል ፈጽሙዋል፣፣ በዚህ የወጣቶች ንቅናቄ ውስጥ ራሱ ወያኔ ሆን ብሎ ባሰማራቸው ቦዘኔዎች ግንባር ቀደምነት ነገሮች ከቁጥጥር ውጭ እንዲወጡና ይህ ነው የማይባል የህዝብ ንብረት እንዲዘረፍና እንዲወድም ተደርጉዋአል፣፣

ገዚው አንጃ በዚህ አላቆመም፣፣ ዛሬ የኢትዮጵያን ህዝብ መፈናፈኛ አሳጥቶ ነጋ ጠባ ላልሞት ባይ ተጋዳይ ትንንቅ እየቀሰቀሰው ያለው ራሱ ገ ው አንጃ የሚከተለው ጸረ ዴሞክራሲ፣ ፍትህ አልባና አፋኝ ፖሊሲ እንደሆነ እየታወቀ ህዝብ ቀሰቀሳችሁ በሚል ሰበብ የተቃዋሚ ድርጅቶችን መሪዎችና አባላት በመግደል፣ በማሰርና በማዋከብ ላይ ይገኛል፣፣ ከፖለቲካ ድርጅቶችም አልፎ የሰብአዊ መብቶች ተሟጋች በሆነው በኢሰመጉ ላይ በከፈተው የማዋከብ ዘመቻ አዛውንቱን የመብት ተሟጋች ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያምንና ዶክተር ብርሃኑ ነጋን አስሮ ኢሰብአዊ በሆነ ግፍ እያሰቃያቸው ይገኛል፣፣ በነጻው ፕሬስ ላይ በከፈተው ዘመቻ ጋዜጠኞች ፥እንዲጠፉ፥ ከማድረግና ከማሰር አልፎ የነጻውን ፕሬስ ውጤቶች በመሸጥ ራሳቸውንና ድሃ ቤተሰባቸውን በሚያስተዳድሩ ወጣቶች ላይ ያፈሳ ዘመቻ በመጀመር እዛው በዛው ነጻና ለየት ያለ ድምጽን ለማፈንና የችግረኛ ቤተሰቦች ጉሮሮ እንዲዘጋ እጅግ ዘግናኝ የሆነ ዘመቻ ከፍ ል፣፣

በነዚህ ክስተቶች ሳቢያ ሃገራችን ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ከቁጥጥር ውጭ ወደሆነ አስከፊ ሁኔታ እየተቃረበች ነው፣፣ ዛሬ ኢትዮጵያውያንን ሁሉ በማስጨነቅ ላይ ያሉ ጥያቄዎች ብዙ ናቸው፣፣ ያንጃዎቹ ትርምስ ጦሱ ለኢትዮጵያ ህዝብ እንዳይተረፍ ምን እናድርግ? የወጣቱም ሆነ ነገ የሰራተኛው፣ የስራ አጡ፣ የገበሬው፣ የነጋዴውና ባጠቃላይ የተቆጣው የኢትዮጵያ ህዝብ የመብት እንቅስቃሴ በወያኔዎች ሴራና በኤጀንት ፕሮቮካተሮች እየተተራመሰና ከቁጥጥር ውጭ እየወጣ ለወያኔዎች የማጥቃት ዘመቻ እንዳይመች ይህ ትግል እንዴት አርጎ ይቀጥልና ይፋፋም? እሷው ጋግራ አልበሰለም እሱዋው ወልዳ አልመሰለም እንደተባለው እነሱው ተቃዋሚ ድርጅቶች እንዳያድጉ አፍነው ይዘው ጠንካራ ተቃዋሚ ድርጅት አጣን እያሉ ሲያሾፉ፣ ትግሉ አቀነባባሪና አስተባባሪ አጣ እንጅ ቀስቃሽ አያስፈልገውም እያሉ ለማቀነባበርና አመራር ለመስጠት የሚ

ሞክሩትን ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በግድያና በእስራት እያንገላቱ ነገሮች ከቁጥጥር ውጭ
ሆኑ እያሉ ሲቀልዱ፣ የሰላምና የዴሞክራሲ አማራጭ ደግሞ ደጋግሞ ቀርቦላቸው እያለ ወያኔ
ዎች ክፍተት ክፍተት እያሉ የሚያቀርቡትን ሰበብና በዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶቻችን ሁሉ ባእዳ
ን ስለዚሁ ክፍተትና ስላማራጭ መጥፋት እያነሱ የሚጥሉትን ጥያቄ እንዴት አርገን እንመልስ?

ኢተፖድህ ባንጃዎች ግጭት መዘዝ አገራችን ወደ ሌላ ትርምስ እንዳትገባ ፥ለሁለ ገብ ቀውስ
ሁለ ገብ መፍትሄ፥ በሚለው መግለጫው ዴሞክራሲያዊና በጎ የመሰለውን የመፍትሄ ሂደት ሲያ
መለክት አንደኛ በተለጣፊዎቹና በባእዳን ሃያላን ድጋፍ ግዜያዊ የበላይነት የያዘው የእነ አቶ መ
ለስ አንጃ በተቃዋሚዎቹ ላይ ምንም አይነት ህገወጥና የሃይል እርምጃ እንዳይወስድ፣ ሁለተኛ
ደግሞ ተቃዋሚው አንጃ በሚያምንበት ፖለቲካ በመላ ሃገሪቱ የመደራጀትና የመንቀሳቀስ መብ
ቱ እንዲከበርለት ጠይቅዋል፡፡

እንዲህ አይነቱ የመብት ትግል የሚካሄደው ሁለቱም አንጃዎች ላለፉት አስር አመታት አብረ
ው መክረውና ዘክረው በህዝባችን ላይ ከተከሉት አስከፊ ስርአት ጋር እንደሆነ ግልጽ መሆን አ
ለበት፡፡ ነገሩ እንደዚህ እስከሆን ድረስ ደግሞ እነ አቶ ስየ በህዝባችን ላይ የተከሉት አገዛዝ
ምንም አይነት ትርጉም ያለው ተቃውሞ የማይፈቅድ ፈላጭ ቆራጭ ስርአት እንደሆነ ተገንዝበ
ው ዴሞክራሲ በመላ ሃገሪቱ እንዲሰፍን ከመታገል ይልቅ የኛ ያንጃዎቹ መብት ተጣሰ፣ የኛ ያ
ንጃዎቹ ሀሳብ በመገናኛ ብዙሃን እንዳይቀርብ ታገደ፣ ለኛ ላንጃዎቹ የህግ የበላይነት ተረገጠ እ
ያሉ ራሳቸው በገነቡት የጸረ ዴሞክራሲ ውቅያኖስ ውስጥ የዴሞክራሲና የህግ የበላይነት ደሴት
ለመመስረት ላይ ታች ሲሉ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በትዝብት እየተመለከታቸው ነው፡፡

ከነዚህ አንጃዎች ግጭት ለኢትዮጵያ መልካም ነገር እንዲወጣ ከተፈለገ የነ አቶ ስየ አንጃና
ደጋፊዎቻቸው በሙሉ ከቀሩት የኢትዮጵያ ዴሞክራቶች ጋር ገጥመው በመላ ኢትዮጵያ ለዴሞ
ክራሲ መታገል ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ ውጭ በመሳሪያ ፍጥጫ ሆነ ፥በውስጣዊ ውይይት፥ ልዩነ
ትን የመፍታት ወይም በሌላ ዘዴ አንዱ ሌላውን አሸንፎ የሚወጣበት ሂደት ያለፈውን ያረጀ ያ
ፈጀውንና የኢትዮጵያ ህዝቦች አክ እንትፍ ያሉትን ስርአትና አገዛዝ የሚያጠናክር አደገኛ ሂደ
ት ነው እንላለን፡፡ ይህ እንዳይሆን ከፈለጉ ደግሞ ዛሬ በሃገራችን የተረጋጋና ዴሞክራሲያዊ ሽ
ግግር ለማረጋገጥ ተቃዋሚ ሃይሎች በሙሉ ለተሰማሩበት ሁሉን አቀፍ ጉባኤና የብሄራዊ ውይይ
ት ጥሪ ከዴሞክራቶች ጋር ወግነው መዋደቅ ይኖርባቸዋል እንላለን፡፡

ይህ የአገር አቀፍ ጉባኤና የብሄራዊ ውይይት ጥሪ ዛሬ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ አንገብጋቢ የ
ሚሆነው ያንጃዎቹን ትርምስ ለሃገራችን በጎ በሆነ ዘዴ ለመፍታት ብቻ አይደለም፡፡ ከሱ ይል
ቅ እጅግ አንገብጋቢ የሚያደርገው ከእንግዲህ በማንኛውም ሰአት እየፈነዱ ከቁጥጥር ውጭ ሊ
ሆኑ የሚችሉ ህዝባዊ አመጾች እየተበራከቱ የሚሄዱበት ሁኔታ በመኖሩ ነው፡፡ እነዚህ ትግሎ
ች መቀጠል አለባቸው፡፡ እኛ ወደድንም ጠላንም፣ ወያኔ ፈቀደም አልፈቀደ ይቀጥላሉ፡፡ የወ
ያኔ መሪዎች የህ ትግል ምንም ቅንብርም ሆነ አግጣጫና አመራር እንዳይኖረውና ለነሱ በሚመ
ች መንገድ እየተተራመሰ እንዲቀጥል ይፈልጋሉ፡፡ ይህ አካሄዳቸው በውስጥም ሆነ ባለም አቀ
ፍ ደረጃ ግልጽ የሆነ አላማ አለው፡፡ በውስጥ ህዝባችን ትግሉ አግጣጫ የለውም፣ አመራር የ
ለውም እያለ ተስፋ እንዲቆርጥና መስዋእትነቱ ሁሉ ከንቱ ነው ብሎ የትግል ትጥቁን እንዲፈ
ታ ለማድረግ ነው፡፡ባለም አቀፍ ኮሙኒቲው አንጻር ደግሞ ጠንካራ አማራጭ የሚሆን ድርጅት
በሌለበት ሁኔታ እኔ ከወደቅሁ አገሪቱ ትተራመሳለች፣ ስለዚህ እየጠላችሁኝም እያፈራችሁብኝ
ም ቢሆን እኔን አቅፋችሁ ደግፋችሁ ከመቀጠል ሌላ አማራጭ የላችሁም እያለ ለማስፈራራት
እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ባጭሩ የወያኔ መሪዎች ህዝባችንንም ሆነ አለም አቀፍ ኮሙኒቲውን ለ
ማሳመን የሚሞክሩት የሽግግር ክፍተት አለ እያሉ ነው፡፡ኢተፖድህ በበኩሉ በተለይ ከፓሪሱ የ

ብሄራዊ ውይይት ጥሪ ወዲህ ለኢትዮጵያ የተረጋጋ ሰላማዊ ሽግግር ለማምጣት ምንም አይነት ክፍተት እንደሌለ ለማስረዳት ሞክሯል፣፣

ይህ የኢተፖድህ ጥሪ ዛሬ በሃገሪቱም ሆነ ባለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነቱ እያደገ መምጣቱ አጠ ያያቂ አይደለም፣፣አለ የሚባለው ወያኔዎች እድሜ ለማራዘም የሚጠቀሙበትን ክፍተት የሚሉት ን ሰበብና የሽግግር አማራጭ አልባ ክርክር መሰረተቢስነት የሚያረጋግጥ ፤*የዴሞክራሲ ሂደትና የነጻ ምርጫ ትልም*፤ የሚለው አሁንም ህያው የሆነ የመታገያ ሰነድ አለ፣፣ ይህ ሰነድ ስለ ነጻ ምርጫ ብቻ አያወራም፣፣ ዋናው ትግሉ በሃገራቸን ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ የሚሰፍንበትንና ዴሞክ ራሲያዊ ሽግግር የሚጋገጠበትን ሁኔታ ለማመቻቸት እንደሆነ በሰነዱ ውስጠ በግልጽ ተቀም ል፣ ፣ይህንን ሂደት ደግሞ የተደራጀና የተቀናጀ መልክ ለማስያዝ ሰነዱ በመጀመሪያ ነጥቡ የሚጠይ ቀው ፤*የዴሞክራሲ ሂደትና የነጻ ምርጫ አካል*፤ ይቋቋም ብሎ ነው፣፣

ሰነዱ የዚህን አካል አላማ ሲዘረዝር በሃገሪቱ ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚከበሩበትን ሁኔታ ለ ማመቻቸት፣ የነጻና ፍትሃዊ ምርጫ መስፈርቶች በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ለመከታተል

ወዘተ እያለ በትክክል አስቀምጧል፣፣ የዚህ አካል አባላት እነማን ሊሆኑ እንደሚችሉ ሲጠቁም ወይ ከዋና ዋና ተወዳዳሪ ድርጅቶች የተውጣጣ ወይ ደግሞ እነሱ የተስማሙበትና ከነሱ ውጭ የተቋቋመ ገለልተኛና በጋራ ስምምነት የተሰየሙ የውጭ ታዛቢዎች ያሉበት አካል ሊሆን እንደ ሚችል ይጠቁማል፣፣

የዚህን አካል ተግባር ባስቸኩዋይ የኢተፖድህ አባል ድርጅቶችና ሌሎችም ሁሉን አቀፍ ጉባኤ እንዲደረግ ጥሪ ያደረጉ ተቃዋሚዎች፣ የሲቪክ ማህበራትና አገር ወዳድ ዜጎች ተወያይተው የ ሚያዳብሩት ቢሆንም በዚሁ በፓሪሱ ሰነድ ላይ ከተጠቀሱት መሃከል የሚከተሉት እንደሚገኙ ከወዲሁ መጠቆም ይቻላል፣

- ዛሬ የወያኔ መሪዎች ለእነሱ ብቻ እንዲመች አውጥተው በተግባር ላይ የሚያውሉዋቸውን የፓርቲ ምስረታና የምርጫ ህግጋት ከጸረ ዴሞክራቲክ ይዘታቸው አጽድቶ ሌላ መሰረታዊ የሆኑ ትን የመደራጀት፣ የመንቀሳቀስ፣ ሃሳብን በነጻ የመግለጽና የማስፋፋት የመሰሉ መብቶችን የሚያ ረጋግጡ ህግጋት አውጥቶ የነዚህን ተግባራዊነት መቆጣጠር

- በሃገሪቱ የህግ የበላይነት የሚረጋገጥበትን ዘዴ ቀይሶ ይህ በተግባር የሚውልበትን ሁኔታ ከ መንግስት ቁጥጥር ውጭ መከታተል

- መገናኛ ብዙሃን በገለልተኛነት ለመላው ህብረተሰብ የሚያገለግሉበትን ዘዴ መቀየስና የፕሬ ስ ህግ የተባለውን ነጻ ፕሬስ አፋኝ ህግ ቀይሮ በሃገራችን ሃሳብ በነጻ የሚንሸራሸርበትን ዘዴ ቀ ይሶ ተግባራዊነቱን መቆጣጠር

- የመንግስት የፋይናንስና የማቴርያል አቅም ስልጣን ላይ ባለው ድርጅት ያላግባብ እንዳይሰ ራበትና ወገናዊ ለሆነ የምርጫ ጥቅም እንዳይውል ተገቢ ዘዴ መቀየስና የዚህንም ተግባራዊነት መከታተል

- የመንግስት ቢሮክራሲ፣ ፖሊስና ሰራዊት በማንኛውም መንገድ ጣልቃ እንዳይገባና የዴሞክ ራታይዜሽኑንም ሆነ የምርጫውን ሂደት እንዳያደናቅፍ ተስማሚ ስትራቴጂ ነድፎ ይህ በትክክል በስራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ የሚሉ ተግባራት ይገኙበታል፣፣

በእርግጥ እነዚህ ሁሉ በሚገባ ተዘርዝረውና በሰፊ ውይይት ዳብረው ገና መልክ መያዝ ይኖ ርባቸዋል፣፣ እዚህ ላይ ግን መጠቆም የምንፈልገው ባንድ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ አማካኝነት እንዲ

ህ አይነቱ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር አካል የማቋቋሙ ጉዳይ ማንም ችላ ሊለው የሚገባው ተግባ ር አለመሆኑን ብቻ ነው፤፤

በዚህ ጉዳይ ከፓሪሱ ጉባኤ ወዲህ የሃገራችን የፖለቲካ ሁኔታ እየተባባሰ በመሄዱ ይህ የብሄራ ውይይትና ያንድ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ ጥሪ በሃገር ውስጥም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ ከእለት እ ለት ተቀባይነቱ እየጨመረ እንደሄደ ግልጽ ነው፤፤ ባለፈው ሰሞን የአውሮፓ ፓርላማ ባሳለፈው ውሳኔ ይህንን ጥሪ የሚደግፍ መሆኑንና የሃገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ ይበልጥ እየተበላሸ እንዳይሄድ ለመከላከል የአውሮፓ ህብረት ይህንን ጥሪ ደግፎ እንዲንቀሳቀስ መመሪያ አሳልፋዋል፤፤ በሃገር ውስጥም ቢሆን ከኢተፖድህ ውጭ ካሉ ድርጅቶች መሃከል የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ) የመ ላ አማራ ህዝብ ድርጅት (መአህድ) የኢትዮጵያውያን ዴሞክራቲክ ፓርቲ (ኢዴፓ) እና ሌሎች ሃይሎች የብሄራዊ ውይይትና የሃገር አቀፍ ጉባኤ ጥሪ አስተላልፈዋል፤፤

ኢተፖድህ ከዚህ በመነሳት ዛሬ በሃገራችን የሽግግር ክፍተት የለም ብሎ ያምናል፤፤ እንዲያው ም በትጥቅ ይሁን በሰላማዊ ዘዴ፣ በህጋዊ መንገድ ይሁን በህቡእ፣ በሃገር ውስጥም ሆነ ከሃገር ውጭ በመንቀሳቀስ ላይ ያሉ ተቃዋሚ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማህበራት፣ ዴሞክራትና አገር ወዳ ድዜጎች ሁሉ ከልዩነቶቻቸው ሁሉ ባሻገር ህብረተሰባችንን በዚህ ዘዴ ወደ ዴሞክራሲ እናሸጋግ ረው ብለው በዚህ አላማ ዙሪያ አጠቃላይ ስምምነት ወይም ኮንሳንሰስ የደረሱበት ወቅት ውስጥ በመገኘታችን ኢትዮጵያን ወደ ዴሞክራሲ ስርአት ለማሸጋገር ከመቸውም ጊዜ የተሻለ አመቺ ሁኔታ ውስጥ እንገኛለን ብለን እናምናለን፤፤

ዛሬ በሃገራችን ሰላማዊ ሽግግር ይቻላል፤፤ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ ይጠራ፤፤ በዚህ ጉባኤ አመካኝነት አንድ ገለልተኛ የሆነ የዴሞክራታይዜሽን አካል ይቋቋም ብለ ን እንታገል እንላለን፤፤ ይህንን ሃሳብ የወያኔ አመራር ላይቀበለው የችላል፤፤ ዴሞክራሲያዊ ተ ቃዋሚ ሃይሎች በዚህ መወናበድ የለባቸውም፤፤ ሂደታቸውን ቀጥለው ግልጽና ዴሞክራሲያዊ የ ሆነ የሽግግር አማራጫቸውን ይዘው ይንቀሳቀሱ፤፤ በሃገሪቱ በመካሄድ ላይ ያለው የገበሬው ሆነ የሰራተኛው፣ የነጋዴው ሆነ የተማሪውና ከሞላጎደል ግብታዊ የሆነው የወጣቱ ትግል፣ ሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች፣ ማህበራዊ ስብስቦችም ሆኑ ነጻው ፕሬስ የሚያካሂዱት ትግልበዚህ ሁሉን አቀፍ ጉባኤና የዴሞክራታይዜሽን አካል መቋቋም ጥያቄ ላይ ያተኩር፤፤

ያኔ ወያኔዎች ትግሉ አግጣጫ የለውም፣ ትርምስ ነው፣ ሃገሪቱን ወደ ጥፋት ሊወስድ ይችላል፣ መስዋእትነቱ ሁሉ ከንቱ ነው እያሉ የህዝባችንን የትግል ትጥቅ ለማስፈታት የሚያደርጉት ፕሮ ፓጋንዳ በመሰረተቢስነቱ ሙሉ በሙሉ ይጋለጣል፤፤ ያኔ ወያኔዎች ክፍተት ክፍተት እያሉ አለ ም አቀፉን ኮሙኒቲ ለማወናበድ የተለቀቁበትን ፕሮፓጋንዳ »የኸው ግልጽ የሆነው፣ በፓሪሱ ጥሪ ተመርኩዞ የዳበረው የሽግግር አማራጫችን» ብለን የክፍተቱን ሰበብ ሙሉ በሙሉ አጣጥለ ንልናጋልጠው እንችላለን፤፤

በመሆኑም ዛሬ አገራችን እጅግ አስቸጋሪና ውስብስብ ሁኔታ ውስጥ እንዳለች ተገንዝበን ሁላች ንም ከህወሃት አንጃዎች ትርምስና ከህወሃት ክፍተት የሚሉ ሰበብ ባሻገር ለብሄራዊ ውይይት፣ ለሁሉን አቀፍና ለዴሞክራታይዜሽን አካል መቋቋም በያለንበት ትግላችንን እጥፍ ድርብ እንድና ደርግ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፤፤

የኢተፖድህ ሴክሬታርየት
ፍራንክፈርት ጀርመን
ግንቦት 28 ቀን 1993 ዓ.ም.